# የቅንጅት ማጅራት መቺዎች

ዓለሙ ኪዳነማርያም
ሲያትል፣ ዋሽንግተን

ከላይ የተጠቀሰውን አርዕስት ከሌላ ድኅረ ገጽ ላይ ማንበቤ ትዝ ይለኛል:: ለወቅቱ በቅንጅት ስም ቅንጅትን ለማፈራረስ የሚጥሩትን ከሃዲዎችና ሆዳሞች አባባሉ ሲገልጽልኝ በመቻሉ ልዋሰው::

አብዛኞቻችን በዘመነ ወያኔ ትግል ውስጥ ስንገባ የዚህን ወያኔ የሚባለውን የዘረኛና የአገር አጥፊ ቡድን በሕዝብ ትግል አስወግደን፣ ሥልጣን የሕዝብ እንዲሆን፣ ሥልጣን ላይ የሚቀመጠው ሕዝብ የመረጠው ሰው እንዲሆን፣ ዲሞክራሲ በአገራችን እንዲጎለብት፣ ሰላም ሰፍኖ ሕዝባችን እንደልቡ ወጥቶ ገብቶ ሰርቶ ከድህነት፣ ከኋላቀርነት ከበሽታ ተላቆ አገራችንን ለማሳደግ ካለን ቅን አመለካከትና የአገር ፍቅር በመነሳት እንደሆነ ይታመናል:: አገር ወዳዱ ጊዜ ገንዘብና ጉልበቱን የሚያፈሰው ለሀገርና ለሕዝብ ባለው ፍቅር ነው::

የወያኔ የዘረኝነት ቫይረስ አልፎ አልፎ አንዳንዶቻችንን እየያዘን ታመን የዳንን እንኖራለን ከነቫይረሱም የምንኖዝም አለን:: አንዳንድ የበሽታ ዓይነቶች ግን በደንብ ስር እንደሰደዱ መገንዘብ ይቻላል:: እነዚህም ራስ ወዳድነት፣ ሆዳምነትና ግዴለሽነት:: ይህ ሆን ተብሎ በወያኔና በሌሎች የውጭ ጠላቶቻችን ቅንብርና ዘመቻ እነዚህ ባህርያት እንዲስፋፉና እንዲለመዱ መደረግ የተጀመረው በኢትዮጵያውያን ዘንድ በሙያቸው፣ በችሎታቸው፣ በእውቀታቸው፣ በታሪካቸው እውቅ የሆኑ ሰዎችን በዘዴ በወያኔ በወጥመድ ውስጥ በማስገባት ነው:: ለምሳሌ አርቲስቶችን፣ ነጋዴዎችን፣ ምሁራንን፣ አትሌቶችንና የአገራችንን ስም በተለያየ መልኩ ያስጠሩትን ወይ በታወቁበት ሙያ አሊያም በተያያዘ መንገድ የወያኔ መሳሪያ እንዲሆኑ በማድረግ ነው:: ይህም እነዚህ የታወቁ ግለሰቦች ከወያኔ ጋር ንክኪ ሲጀምሩ ወይም የወያኔ መሳሪያ ሲሆኑ ሕዝብ ያዝንባቸዋል፣ ይሸሻቸዋል:: ሕዝብ ሲጠላቸውና ሲሸሻቸው ደግሞ ያንን ለመተካት በገንዘብ ኃይል የሕዝብን ፍቅር ይለውጣሉ:: ገንዘቡ ደግሞ ጊዜያዊ እንጂ ዘላለማዊ ስላልሆነ ወያኔ የተወሰነ ጊዜ ከተጠቀመባቸው በኋላ ገሸሽ ያደርጋቸዋል:: ማለትም ወያኔ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መታ ማለት ነው:: አንድም የኢትዮጵያን ስምና ክብር የሕዝብን ፍቅርና አክብሮት የተላበሱትን በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከሕዝብ እንዲለያዩ ያደርጋል ስለሆነም የነበራቸው ኢትዮጵያዊ ዝናና ክብር ሁሉ ይጠፋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያን ያስጠሩና የሚያስጠሩ ሰዎች ሆዳሞችና ስግብግቦች ሆነው ሕዝብ ሲያገኛቸው ሕዝብ ተስፋ ይቆርጣል ሌላውም በእነርሱ እግር ያለው የእነርሱን ፈለግ ለመከተል ይሞክራል:: ድሮ ማንም ባለሞያ፣ ልዩ ችሎታ ያለው ወይም ተሰጥኦ ያለው ለሀገሩና ለሕዝቡ ሲል ነበር በተሰለፈበት ሙያ ከፍተኛውን ደረጃ ለማግኘት የሚጥረው:: የአገሩን ስም ማስጠራት ባንዲራውን ከፍ አድርጎ እንዲውለበለብ ማስደረግ ነበር ከፍተኛ ፍላጎቱ:: ዛሬማ "ያ ድሮ ቀረ" ማለት ተጀምሮ ለጌታው አቶ ብሩ ማጎንበስ እና መገዛት ሆነ ፋሽኑ:: አሳፋሪና አሳዛኝ ምግባር ነው::

እስቲ ዛሬ ሕዝባቸው ሲሰቃይ፣ በወያኔ አገዛዝ ሲማቅቅ፣ ሲገደል፣ በየወህኒ ቤቱ ሲጣል አገሬ አገሬ ይሉ የነበሩት የቀድሞዎቹ ዝነኛ ድምጻውያን ዛሬ የታሉ? አገር መውደድ የዓውድ ዓመት ወይም የበዓላትን ስም መጥቀስና የድሮው ዳቦ፣ የጠላውና የዶሮ ወጡ ትዝታን ማላዘን ብቻ ነው? ያ ጀግናና ኩሩ ሕዝብ ሲሰቃይ፣ ሲዋረድ፣ አንድነቱና አገሩ አደጋ ላይ ሲወድቁ ሼራተን ሆቴል መዝፈን ብቻ ነው እንዴ የሚያውቁት? አትሌቶቻችንስ የት አሉ? የመንፈስ አባቶቻችን? ምሁራኖቻችን? አገራችን ያስተማረቻቸው ሀኪሞችስ? ከፍተኛ እውቀት ያላቸው መሀንዲሶች ወዴት ገቡ? ለምንድነው ለወያኔ ብቻ ዘጥ ዘጥ የሚሉት ድምጽ ብቻ የሚሰማው? የሕዝባችን እዳ ያለብን ሰዎች ዛሬ ኑሮአችንን ብቻ ስንመለከት አገራችንንና ድሃ ሕዝቧን የሚመለከትና የሚቆረቆር ምነው ቁጥሩ አነስተኛ ሆነ? ለራስ ጥቅምና ዝና ካልሆነ በቀር ምነው ለእውነት የሚቆም አልታይ አለ? ፈሪው በዛሳ፣ አድር ባዩ ግፊያው አላድርስ አለ ለምን ይሆን ? መልሱ ቀላል ነው:: ወያኔ በገንዘብ ስለገዛው ነው:: የሥልጣን ፍርፋሪ መለቃቀም እንደ ትልቅ ነገር ቆጥሮት በአገር ማጥፋቱ ስራ ላይ ከወያኔ ጎራ መሰለፍ እንደ ፋሽን በመቆጠሩ ሲሆን፤ ሌላው ወያኔ በፈጠረው የስነልቦና ጦርነት አንገቱን ደፍቶና በየቤቱ ተደብቆ ያለው ክፍል ደግሞ ተስፋ ቆርጦና ፍራቻ ነግሶበት መስዋዕትነት ለመክፈል ድፍረቱን አጥቶና ሐሞቱን አፍስሶ ወያኔን መታገሉን ችላ በማለቱ ነው:: አገራችንን ከጥፋት ለማዳን የሁላችንም ርብርቦሽ ይጠይቃል:: አገራችን ትጥፋ ምን አገባን ለሚሉት ሆዳሞችና ግዴለሾች ደግሞ የምንላቸው አለ፤ ቆራጥና ጀግና ልጆች

ኢትዮጵያ ስላሏት አትጠፋም እናንተ አወዳደቃችሁ አያምርም እንጂ:: እነዚህ ግለሰቦች ሆዳቸውን እየሞሉ ዘላለም በሰላም የሚኖሩ እንዳይመስላቸው:: ድብልቅልቁ ይወጣል ሆዳሙና አድር ባዩ እየተጋለጠ ከወያኔ እኩል ለፍርድ ይቀርባታል እንጂ ወንጀላቸው ተደብቆ አይቀርም:: በገንዘብና በፕሮፓጋንዳ ኃይል ወያኔ የተጠናከረና ብዙ ደጋፊ ያለው ይምሰል እንጂ ሕዝባችን እንደ ሚያዝያ 30ው ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ቁጣውን የገለጸ ቀን እናንተን አያድርገን እንላለን:: ያ ደግሞ መሆኑ አይቀሬ ነው:: አሁን የተጀመረው ከሃዲውና ሆዳሙ ከዚህ አሳፋሪ ምግባሩ እንዲታቀብ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መስጠት ነው:: አልሰማ ያለው እንግዲህ ለሕዝብ የፍርድ ቀን ያድርሰው እንላለን::

ወደ አርዕስቴ ልመለስ:: የዘንድሮ ከሃዲዎችና ሆዳሞች ያለፉትን ሁለት ዓመታት ውስጥ ውስጡን ሲዶልቱት የነበረውና በተላላኪዎቻቸው በእነ አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ በኩል ሲያደርጉት የቆዩት የተነገራቸውና የጠበቁት ዓይነት ውጤት ስላላመጣላቸው አይናቸውን በጨው አጥበው እራሳቸው ተነከሩበት:: አዬ ቅሌት:: አዎን መሪዎቻችን ብለን ስንጮኽላቸው የነበሩት የውጭና የወያኔ መሳሪያዎች መሆናቸውን ዛሬ በይፋ እያሳዩን ነው:: የእነርሱ ተላላኪዎች ደግሞ አድርጉ የተባሉትን ያደርጋሉ:: በየከተማው እየዞሩ ይቀላምዳሉ፣ ይዋሻሉ አሉባልታ ይነዛሉ:: ይህ የዘመናችን አሳፋሪ ምግባር ነው::

እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እንደ አምላክ እንዲመለኩ ለማድረግ የእነ አንዳርጋቸው ቡድን ሲያካሂዱ የነበረውን መጠነ ሰፊ ቅስቀሳ አንዘነጋም:: የእነ አንዳርጋቸውና ብርሃነ መዋ የአንድ ዓመት ተኩል ውንብድናና ግራ ማጋባት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ በሀቀኞች ድባቅ ተመትቶ እነ ብርሃኑ ነጋን ከእነጭፍሮቻቸው እርቃናቸውን እንዲቀሩ አድርጓቸዋል:: በሀሰትና በስም ማጥፋት የተሸፈነው ስራቸው ለእውነትና ለሀቅ በቆሙት ጀግኖቻችን መጋረጃው ሲገለጥ እነማን ምን እንደሆኑ ቁልጭ አድርጎ አሳዬን:: የአፈንጋጩ ቡድን ከማን ጋርና ለማን እንደቆመ ለየለት:: ሽምግልና፣ ድርድር፣ ውይይት፣ እርቅ የሚባሉት ሰላማዊ መንገዶች በእነብርሃኑ ነጋ ቡድን አሉባልታ፣ ስም ማጥፋት፣ ክህደት፣ ወያኔነት ቦታ ሊያገኙና ሊሰሩ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ:: እነርሱ ለሕዝብ ፍርድ እንጂ ውይይትና ድርድር የሚቀርቡ አይደለም:: ምክንያቱም ዓላማቸውና መንገዳቸው ከድሮም ጀምሮ ከጠላት ጋር የወገኑ ቅጥረኞች በመሆናቸው ነው:: በቃሊቲ የቆዩበት ጊዜ የሚታሰበው የቅንጅት ስራ እስኪዳከም፣ አንዳንድ ደካማ አቋም ያላቸውን በገንዘብና በጥቅም ደልልው ወደ እነርሱ ጎራ እስኪያስገቡ ድረስና በውጭ ያለው የድጋፍ ኃይል እስከሚከፋፈልና እስከሚዳከም ድረስ ነው::

የአፈንጋጩ ቡድን አሜሪካ መጥቶ በዳላስ እንዳየነው ለአምስት ልዑካን ተብዬዎች ሰድስት ሊሞዚኖች ተደርድሮላቸው ጉሮ ወሸባዬ ተዘፍኖላቸው የዘራፈፉትን ዘራርፈው ሲጨርሱ ፊሪ ለእናቱ አሜሪካ ሲቀር ሌላው አገር ቤት ተመልሷል:: ታዲያ የዛሬ የብርሃኑና የደበበ እሸቱ በየከተማው እየሄዱ የሚያደርጉት መወራጨት ትርጉም አልባ ሆኖ ከማሳፈርም በላይ ሆኗል:: ለመሆኑ መካሪም ሰው የላቸውም ወይ ያሰኛል:: በእያንዳንዱ ድርጊታቸው ላይ ጥፋታቸው እየባሰባቸው፣ እየተደናበሩ፣ እየዋሹ፣ ወያኔያዊ ስራቸውን መቀጠል ተያይዘውታል:: ዛሬ ግን ሕዝብ ሐቁን አውቆ "የቅንጅት" ጨምበላቸው ሲወልቅ የወያኔ ጥብቆ እንደለበሱ በስራቸው አረጋግጠዋል::

ዶክተር ብርሃኑ 22 ሰው በተገኘበት ስብሰባው ላይ መጥቶ 17 ገፅ ዕሑፍ ያነባል ልጅ ስለመውለዱና ስላለመውለዱ፣ መጽሐፍ ስለመጻፉና ስላለመጻፉ ያትታል:: ኢትዮጵያውያን ያንን ለማዳመጥ ፍላጎትና ጊዜ የላቸውም:: የቅንጅት መከፋፈል ዋነኛው ተጠያቂና ሴረኛው፣ የስልጣን ጥመኛው፣ ከሃዲው የውጭ መንግሥት ቅጥረኛና የወያኔ ወዳጅ የብርሃኑን ነጋን ማንነት ሕዝብ አውቂል:: የብርሃኑ ነጋ ከወያኔ የተጋባበት የዘረኝነት ቫይረሱን እዚያው ባጥቢያው ለራሱ ይያዘው:: ከምርጫው በፊት የነበረውን ታሪክ እድሜ ለፕሮፌሰር መስፍን ተሸፍኖለት፣ እንዲያውም የሕዝብ ሰላማዊ አመጹን ከበየነ ጴጥሮስ ጋር ሆኖ ከቅንጅት አመራር እውቅና ውጭ ያኮላሸ ጊዜ ነበር ስራውን በተግባር ማሳየት የጀመረው:: የዛሬው እንቅስቃሴው የወያኔን እድሜ በምርጫ 2010 ስም ለማራዘም ነውና አራዳነትህ በዚሁ ያብቃ ብለነዋል:: ያለቀለት ጉዳይ ነው::

ሌላው በሬውን ለማከል እንደምትሞክረዋ እንቁራሪት በወሬና በውሸት ጉራ እያበጠ ያለው አቶ ደበበ እሸቱ ነው:: አቶ ደበበ እሸቱ ልጁን ለመጠየቅ እንደመጣ ወዳገሩ ቢመለስ ይሻለው ነበር:: ያንን ባለማድረጉ ዛሬ ጉዱ እየወጣ ነው:: ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን እርሱ በምንም ዓይነት ሁኔታ ሊመጥን ቀርቶ ሊታሰብ የማይችለውን ታላቅ መሪ በየሄዱበት ከተማ ዱካቸውን እየተከተለ ጥላሸት

እቀባለሁ ሲል ይበልጥ ይሳቅበታል፣ የበለጠም እራሱን እያዋረደ ነው፡፡ ቅንጅት እንዳንተ አይነቱን ቅሌት ባንገቱ ማሰባሰቡ ሲያሳፍር፣ አንተን እዚያ ያስገባህ ሰው ቅንጅትን እንዴት ማጅራት መመታት እንደምትችል እርግጠኛ መሆኑን አረጋግጦ መሆን አለበት፡፡ በነገራችን ላይ ሎስ  አንጄለስ በ94 ነው 95 ዓ.ም የመጣህ ጊዜ አገር ቤት ለቤተሰቦቻቸው እንድትሰጥላቸው 5000 የአሜሪካን ዶላር ሰጥተሀው የውሃ ሽታ አድርገህ ያስቀረህባቸው ሰዎች ጉድህን በአደባባይ ያወጡልሃል፡፡ ምን ለምን ነው አብረህ አዝግም ያለው ያገሬ ሰው፡፡ አንተና አለቃህ ብርሃኑ ነጋ ማፈሪያዎች ናችሁ፡፡ ሶስትና አራት ሰዎች የሰጡህን የአደራ ገንዘብ የበላህ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዴት ነው ልታስተዳድር የምታስበው፡፡ በትንሹ የታመነ በብዙው ይሾማል ይላል መጽሐፉ፡፡ ለራስህ፣ ለቤተሰቦችህ፣ ለቅንጅትና ለኢትዮጵያ ማፈሪያ ሆንክ፡፡ ለከተማችን ለሲያትልም ማፈሪያ ነህና ቅርብን፡፡ አንፈልግህም፡፡ አገር ቤት የሰራሃቸው ወንጀሎችና ምግባረ ብልሹ ስራዎች በቅንጅት ስም ተሸፍነው ይቀራሉ ብለህ እንዳታስብ ተከትለውህ ማንነትህን ያጋልጣሉ፡፡

የቅንጅት አመራር በእንደዚህ ዓይነት ጸረ ቅንጅት በሆኑና ማፈሪያ በሆኑ ግለሰቦች ላይ በአፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ በአሳፋሪ ድርጊታቸው የቅንጅትን ስም ክፉኛ አጉድፈውታል፡፡ ዋናው ዓላማቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የደገፈውንና መስዋዕት የከፈለበትን ቅንጅት ማዋረድ፣ መከፋፈልና ማጥፋት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የወያኔ ዋናው ዓላማው ነው፡፡ ሕዝብ ቅንጅት እንዲህ ነው እንዴ በማለት ተስፋ እንዲቆርጥ የተደረገ ታላቅ ሴራ ነው፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ዶክተር ብርሃኑን አመቻቹትና የጥፋት ቀስታቸውን ወረወሩ፣ ቀስተ ደመና በማለት፡፡ አጅሬ ደግሞ ብጤዎቹን በወያኔ የዘረኝነት ቫይረስና መርዞና በገንዘብ ገዝቶ እና እነብርቱካንን፣ ደበበ እሸቱን፣ አንዳርጋቸው ጽጌን እና ሌሎች ከሃዲዎችን በግሉ በማምጣት አስቀመጠ፡፡ ማጅራት መቺዎቹ መጀመሪያ በውጭ አገር ተሰማርተው የቻሉትን ያህል መታቱ፡፡ በገንዘብ የገዟቸው የሬዲዮ፣ የቴሌቭዥን፣ የድኅረ ገጽ እና የፓልቶክ ክፍሎችን አማካኝነት ቅንጅትን ማጅራት ማስመታት ጀመሩ፡፡ በልዑካንም ስም ይሸው ማጅራት መቺው ክፍል ቀን በቀን በሊሞዚን ተንፈላሰው በእነ ታማኝ በየነ አስተናጋጅነት የቅንጅትን ደጋፊዎች ማጅራት መቱና የዘረፉትን ሰባስበው ደጋፊውን ከፋፍለው አበቁ ስንል አሁን ደግሞ ሁለተኛ ዙር ሊጀምሩም ቢያስቡ ሕዝብ አውቋቸዋልና እንደበፊቱ አይታለልላቸውም፡፡ ሕዝብ እየተናደደባቸው ደጋፊዎች የነበሩት ግራ እየተጋቡና አንዳንዶቹ ወደ እውነት እየተመለሱ ነው፡፡

ተስፋ የሚሰጠው የአንድነት ኃይሎች እየተሰባሰቡና እየተጠናከሩ ቀጣፊውንና መሰሪውን እያጋለጠ እየተዋጋ አገሩንና ሕዝቡን ለማዳን እየታገለ ይገኛል፡፡

ዛሬ የብርሃኑ አንጃ፣ የኢሕአፓ አንጃና የወያኔው የሰዬ አብርሃ ቡድን ጸረ ኢትዮጵያ ሴራና ጥፋታቸውን ሊዘረጉብን ውስጥ ለውስጥ ሲዶልቱብን የአንድነት ኃይሉም ክፍል ደግሞ ተንቀሳቅሶ አሳፈሮና አጋልጦ ድባቅ እየመታቸው ይገኛል፡፡ ያለን አማራጭ ከአንድነት ኃይሉ ጎን መቆም ነው፡፡ ከእውነት ጋር ቆሞ ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ይሻላል ለጊዜያዊ ጥቅም ተገዝቶ የሕዝብ ትግልን ማጅራት ከመምታት፡፡

የአንድነት ኃይሉ ትግል ይቀጥላል!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!